# በቅናሽ ወይም ያለ ምንም ወጪ የጤና ሽፋን ያግኙ

## Kaiser Permanente's Community Health Access Program (CHAP)



ሁሉም እቅዶች በ Kaiser Foundation Health Plan of the Mid-Atlantic States, Inc., 2101 E. Jefferson St., Rockville, MD 20852 ሀላፊነት የሚቀርቡ ናቸው

## አሁን ሽፋን በአቅራቢያዎ ይገኛል

የማህበረሰብ ጤና መዳረሻ ፕሮግራሙ (CHAP) ማንኛውም ሌላ የጤና ሽፋን ማግኘት ለማይችሉ ልጆች እና ለወጣቶች ነው። እና ብቁ ለመሆን የግድ የዩኤስ ዜጋ መሆን የለብዎትም—ሰነድ የሌላቸው ኗሪዎች ለማመልከት ተቀባይነት አላቸው።

## የ CHAP አባላት የ Kaiser Permanente plan Maryland (MD) Gold Value 0/20/Vision ወይም Virginia (VA) Gold 0/20/Vision ዕቅድ ያገኛሉ[1]

- ወርሃዊ የአባልነት ክፍያ አይከፍሉም።
- በ Kaiser Permanente ተቋማት ዝቅተኛ ይከፍላሉ ወይም ለአብዛኛው ሽፋን ክፍያ አይከፍሉም።

## ብቁ ነኝ?

**ለ CHAP ብቁ ነዎት የሚከተለውን ካሟሉ፦**

- የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሳያጠቃልል በ Kaiser Foundation Health Plan የ Mid-Atlantic States, Inc.፣ የገበያ አካባቢ ውስጥ የሚኖሩ ከሆኑ
- በፌደራል የድህነት ደረጃ ገቢ እስከ 300% የሚደርስ ቤተሰብ የሚኖሩ ከሆነ
- እንደ Medicaid፣ Medicare፣ ስራ መስረት ያደረገ የጤና ዕቅድ ወይም Maryland Health Connection (በ Maryland ውስጥ) ወይም የጤና ጥቅማጥቅም ልውውጥ (በ Virginia ውስጥ) የመሳሰሉ በነሱ ብቻ ሳይወሰን ሌላ የመንግስት ወይም የግል የጤና ሽፋን ብቁ ካልሆኑ



## አኗኗሬ ከተለወጠ ምን ይሆናል?

CHAP ላይ ለመቀጠል በየአመቱ እንደ አዲስ ማመልከት ይኖርቦታል። የማያሟሉ ከሆነ፣ እናሳውቅዎት እና ከ CHAP የድጎማ ፕሮግራም ምዝገባ እናስወጣዎታለን። ከዚያ በኋላ፣ ለ Kaiser Permanente MD Gold Value 0/20/Vision ወይም VA Gold 0/20/Vision ዕቅድ[1] እንዲሁም ላገኙዋቸው አገልግሎቶች ከኪስ ውጭ ወጪዎች—ከ HMO ዕቅድ አባልነትዎ እንድንሰርዝዎ ካልጠየቁን በስተቀር መደበኛ ወርሃዊ የአባልነት ክፍያዎች መክፈል አለብዎት።

# ጤናማ መጪ ጊዜ እዚህ ይጀምራል

የማህበረሰብ የጤና መዳረሻ ፕሮግራሙ ወርሃዊ የአባልነት ክፍያዎን እና ለልጆች እና ለወጣት አዋቂዎች አብዛኛውን ከኪስ የህክምና ወጪዎች ለመክፈል እንዲያግዝዎ ድጎማ ይሰጣል።

## ጥቅማጥቅሞች በጨረፍታ[1]

| ከ Kaiser Permanente Maryland (MD) Gold Value 0/20/Vision ወይም Virginia (VA) Gold 0/20/Vision ዕቅድ ጥቅማጥቅሞች ጋር | ከ CHAP ጋር (በ Kaiser Permanente ተቋም ለአገልግሎቶች) ከኪስ ወጪዎች |
|---|---|
| የመከላከል የጤና እንክብካቤ/ማጣራት/ክትባት | $0 |
| የመጀመሪያ የጤና እንክብካቤ የጽሕፈት ቤት ጉብኝት | $0 |
| ለልዩ የጤና እንክብካቤ የጽሕፈት ቤት ጉብኝት | $0 |
| በሐኪም ትእዛዝ የሚወሰዱ መድሀኖቶች (የ Kaiser Permanente እቅድ መድሀኒት ቤት ወይም በፖስታ ትእዛዝ አገልግሎት አማካኝነት ለ30-ቀን የሚበቃ ማግኘት ይቻላል[2]) | $0 |
| የአእምሮ የጤና አገልግሎቶች | $0 |
| የአስቸኳይ የጤና እንክብካቤ | $0 |
| የአደጋ ጊዜ ክፍል አገልግሎቶች | አገልግሎቶች ባገኙበት ቀን መክፈል ያለብዎ ክፍያ ድርሻ ወይም የመድህን ድርሻ ሊኖር ይችላል |
| የሆስፒታል ቆይታ (ክፍል/የሃኪም ክፍያዎች) | $0 |
| አብዛኞቹ ኤክስ-ሬዮች | $0 |
| የበጎ ሁኔታ ክላሶች[3] | ብዙ ያለ ምንም ክፍያ ለአባላት |


## የሚፈልጉት የጤና እንክብካቤ፣ የሚፈልጉት መንገድ



ለእርስዎ አስፈላጊ የሆነውን ምርኩስ በማድረግ ከሚነገሩ ቋንቋዎች እስከ ትምህርት እና የህክምና ስፐሻሊቲ የእርስዎ ወይም የእርስዎ ልጅ ሃኪም ይምረጡ።



አስቸኳይ ያልሆኑ ጥያቄዎችን ለራስዎ ዶክተር ወይም ለልጅዎ ዶክተር በኢሜይል ይላኩ፣ ወይም የስልክ ቆጠሮ አለያም የቪድዮ ጉብኝት ቀነቀጠሮ ይያዙ።[7]



የራስዎን ወይም የልጅዎን ጤንነት የትምብቦታ ሆነው ያስተዳድሩ—አብዛኞቹን የላብራቶሪ ምርመራ ውጤቶችን ይዩ እንዲሁም አብዛኞቹ በትእዛዝ የሚሞሉ መድሀኒቶችን በኦንላይን ወይም በመተግበሪያ ይዘዙ።[4,5,6]



በአንድ ጣራ ስር እንድ ኤክስ-ሬይ እና ፋርማሲ የመሳሰሉ ብዙ አገልግሎቶችን ጊዜ ይቆጥቡ።

# በማህበረሰብ ጤና መዳረሻ ፕሮግራም (CHAP) መመዝገብ

## እንዴት ማመልከት ይችላሉ

**እነዚህን ሰነዶች ይሙሉ፡**

- የድጎማ ብቁነት ቅጽ
- የጤና ሽፋን ማመልከቻ

የገቢ ማረጋገጫ እና እላይ በቅጾቹ ውስጥ የተዘረዘሩ ማንኛውም አስፈላጊ ሰነዶችን ያካትቱ።

እባክዎ ለምዝገባ መረጃ የተመደበው የአካባቢ ማህበረሰብ ድርጅት ያነጋግሩ።

> **ማስታወሻ:** በአካባቢዎ ከሚገኝ የተመደበ የማህበረሰብ ድርጅት ጋር ሳይሰሩ CHAP ላይ መሳተፍ አይችሉም።

የግል መረጃዎን በህግ እንደሚፈለገው በግላዊነት እንይዘዋለን እና እርስዎ ለፕሮግራሙ ብቁ ከሆኑ ብቻ ለማየት እንጠቀመዋለን።

## በክፍት የምዝገባ ወቅት ያመልክቱ

**አብዛኛው ጊዜ፣ ከኖቬምበር 1 እስከ ዲሰምበር 15 ባለው ነጻ የመመዝገብያ ጊዜ ውስጥ ለ CHAP ማመልከት ይኖርቦታል።**

**ጃንወሪ 1 ላይ ሽፋን ለመጀመር፣ በዲሰምበር 15 የተሞላ የወረቀት ስራዎትን መቀበል ይኖርብናል።**




**ጥያቄዎች? ተጨማሪ ለማወቅ፦**

በ **800-777-7902** (TTY **711**)፣ ከሰኞ እስከ ዓርብ 7:30 ጠዋት እስከ 9 ከሰዓት (በዋና በዓላት ዝግ ነው) የአባል አገልግሎቶች ይደውሉ።

Visit **kp.org/mas-chap**.

**በማህበራዊ ሚዲያ ይከተሉን፦** @kpthrive

የ CHAP ብቁነት ቀጣይ ዋስትና የለውም። ምዝገባን ለመዝጋት ወይም የ CHAP ብቁነት ደንቦችን በማንኛውም ጊዜ የመለወጥ መብታችን የተጠበቀ ነው። ለ CHAP ድጎማ ብቁ ከሆኑ፣ የድጎማው ብቁነት ውሱን ነው እና አሁንም ብቁ መሆንዎን ለማረጋገጥ በመጪው ጊዜ እናገኝዎታለን።

---

[1]እባክዎ የውሁድ አባልነት ስምምነቱን፣ የመግለጫ ቅጹን እና ውስንነቶች እና ልዩነቶች የሽፋን መረጃ ያጣቅሱ። የ Maryland (MD) Gold Value 0/20/Vision ወይም የ Virginia (VA) Gold 0/20/Vision ዕቅድ የጥቅማ ጥቅሞች እና የሽፋን ማጠቃለያ *(SBC)* በመስመር ላይ ይገኛል እና የጤና ዕቅዱን ዝርዝሮች ያጠቃልላሉ። ወደ **kp.org/sbc** ይሂዱ እና በካርታው ላይ የእርስዎን ስቴት ጠቅ ያድርጉ። ከዚያ፣ በ**2022 በ Kaiser Permanente የቀረቡ ዕቅዶች**፣የMD Gold Value 0/20/Vision ወይም VA Gold 0/20/Vision የሚለውን እቅድ ጠቅ ያድርጉ። ያለ ምንም ክፍያ ለወረቀት ቅጂ፣ **800-777-7902** (TTY **711**) ይደውሉ። በ CHAP የተሸፈኑ ከሆኑ፣ በ *SBC* የተዘረዘሩ Copays፣ ለአብዛኞቹ እንክብካቤ በ Kaiser Permanente ተቋማት ተግባር ላይ አይውሉም።

[2]አንዳንድ መድሀኒቶች በፖስታ ትእዛዝ ሊሰጡ የሚችሉ አይደሉም። በፖስታ የሚታዘዙ መድሀኒቶች የሚሰጥ መድሀኒት-ቤት MD, VA, DC ወደ ሚገኙ አድራሻዎች እና ከአገልግሎት ቦታ ውጪ ወደ ሚገኙ አንዳንድ ቦታዎች ማድረስ ይችላል።

[3]አንዳንድ ክላሶች ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ።

[4]እነዚህ አይነቶች የ Kaiser Permanente ተቋማት ላይ ሲታከሙ ብቻ የሚገኙ ናቸው።

[5]ህጻናት እድሜያቸው 12 አመት ሲሞላቸው የኦንላይን አይነቶቹ ይቀየራሉ። በመንግስት ህግ መሰረት በአሥር እና አስራ ዘጠኝ መካከል ያሉ ጎረምሶች ለተጨማሪ የግላዊነት ጥበቃ ይገባቸዋል። ልጅዎ 12 ዓመት ዕድሜ በሚደርስበት ጊዜ፣ ለአንዳንድ ባህሪያት የተሻሻለ መዳረሻ በማድረግ ለጎረምሳው እንክብካቤ ማድረግ ይችላሉ።

[6]የ Kaiser Permanente መተግበሪያ ለመጠቀም፣ **kp.org የተመዘገቡ የ Kaiser Permanente አባል መሆን ይኖርቦታል።**

[7]ተገቢ በሚሆንበት እና በሚኖርበት ጊዜ።

Kaiser Foundation Health Plan of the Mid-Atlantic States, Inc.
2101 E. Jefferson St., Rockville, MD 20852  2022CH1574AM MAS 10/28/22-12/31/23